# ዩኤንዲፒ የፍላጎት መግለጫ
# ለቅድመ ማጣሪያ ሒደት ተሳትፎ የቀረበ ጥሪ

ዩኤንዲፒ ኢትዮጵያ ለኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የቴክኒክ ድጋፍ ለሚሰጠው ለኢትዮጵያ ዴሞክራሲ መጠናከር ምርጫዎችን መደገፍ ወይም Supporting Elections for Ethiopia's Democracy Strengthening (SEEDS) ለተባለው ፕሮጀክቱ ዕቃዎችና አገልግሎቶችን ለማቅረብ ፍላጎት ያላቸው ድርጅቶችን ድርጅቶች ለመጋበዝ ይፈልጋል። ፕሮጀክቱ ምርጫው በሚካሄድበት ጊዜ ሁሉ በሚከናወኑ የምርጫ ስራዎች በርካታ መስኮች ላይ የቴክኒክ ድጋፍ ያቀርባል። የዚህ የማስታወቂያ ጥሪ ዓላማ ከዚህ በታች በተዘረዘሩት መስኮች ላይ ፍላጎት ያላቸውን ድርጅቶች ለመለየትና መስፈርቱን የሚያሟሉትን ድርጅቶች አስቀድሞ የመለየት ሒደት ለማከናወን ነው። በቅድሚያ መስፈርቱን የሚያሟሉ ድርጅቶች ብቻ የጨረታ ሰነድ እንዲያቀርቡ ይመረጣሉ።

አቅራቢው ከሚከተሉት መስኮች በአንዱ ወይም ከአንድ በላይ ዕቃዎች/አገልግሎቶችን ያቀርባል፡-

1. የሕትመት ስራዎች EOI-SEEDS-01-2020.
2. መልቲሚድያ ፕሮዳክሽን EOI-SEEDS-02-2020.
3. የሚድያ አየር ሰዓት ምደባ አገልግሎቶች EOI-SEEDS-03-2020.
4. በመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ ቅስቀሳዎችን መከታተል EOI-SEEDS-04-2020.
5. የጥሪ ማዕከልና የአጭር የጽሑፍ መልዕክት አገልግሎቶች EOI-SEEDS-05-2020.
6. የማሕበራዊ ሚድያ አገልግሎቶች EOI-SEEDS-06-2020.
7. የመዝናኛ አገልግሎቶች EOI-SEEDS-07-2020.
8. የሕዝብ አስተያየት መሰብሰቢያ የዳሰሳ ጥናቶች EOI-SEEDS-08-2020.
9. ኤቨንት ማኔጅመንት እና ክንውን EOI-SEEDS-09-2020.
10. የሰው ሐብት አስተዳደር EOI-SEEDS-10-2020.
11. የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ (አይሲቲ) አገልግሎቶች EOI-SEEDS-11-2020.
12. የሎጂስቲክስ አገልግሎቶች EOI-SEEDS-12-2020.

**የቅድመ ማጣሪያ መስፈርቶች፡-**

የቀረቡ ሰነዶች ሙሉ መሆናቸው የሚጣራ ሲሆን፣ በዋነኛነት በሚከተሉት መስፈርቶች ላይ በመመስረትም ብቁነትን ለመመዘን ያገለግላሉ፡-

| EOI ቁጥር | አገልግሎቶች | የሚፈለጉ አገልግሎቶች ዝርዝር | የብቃት መስፈርት |
|---|---|---|---|
| UNDP-SEEDS-01-2020 | የሕትመት አገልግሎቶች | የመራጮች ማስተማሪያና ማሰልጠኛ ማቴሪያሎችን በከፍተኛ መጠን ማተም ያስፈልጋል። በዚህም ውስጥ የሚካተቱ ስራዎች፡- ማንዋሎችና መመሪያዎችን፣ በራሪ ወረቀቶችን፣ ፖስተሮችን፣ ብሮሸሮችን፣ ባነሮችን፣ ሮል አፐስ፣ ፍሊፕ ቻርቶችን፣ የመረጃ ጥራዞችን፣ ቲሸርቶችን፣ ኮፍያዎችን፣ እስክሪብቶ፣ የቀን መቁጠሪያዎች፣ ተለጣጭ የእጅ ብራስሌቶችን፣ ወዘተ... ማተም። | • ቢያንስ የ3 ዓመት ልምድ ያለው<br>• በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኮፒዎችን በአጭር ጊዜ ውስጥ ለማተም የሚያስችል ግዙፍ የፕሮዳክሽን አቅም ያለው<br>• የቀረቡት ናሙና ማቴሪያሎች ጥራት ወሳኝነት አለው<br>• ከ $50,000 (ሃምሳ ሺህ ዶላር) በላይ ዋጋ ያላቸውን 3 ግዙፍ ኮንትራቶች ከዚህ በፊት ያከናወነ መሆን አለበት |
| UNDP-SEEDS-02-2020 | መልቲሚድያ ፕሮዳክሽን | በፈጠራ የታገዙ የራዲዮ፣ ቲቪ እና የሕትመት ማስታወቂያዎችን፣ ፕሮግራሞችን፣ ጂንግሎችን፣ ቢልቦርድ፣ የማስታወቂ ቦርድ ወዘተ... ለመራጮች ትምህርት ዘመቻ አስፈላጊ ናቸው። | • ቢያንስ የ3 ዓመት ልምድ ያለው<br>• የቲቪ፣ ራዲዮና የሕትመት ማስታወቂያዎችን የማዘጋጀት የኦዲዮ/ቪድዮ ፕሮዳክሽን አቅም ያለው መሆን አለበት<br>• በክልላዊ ቋንቋዎች የማዘጋጀት ልምድ ያለው |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | | • የቀረቡት ናሙና ማቴሪያሎች ጥራት ወሳኝነት አለው<br>• ከ $30,000 (ሰላሳ ሺህ ዶላር) በላይ ዋጋ ያላቸውን 3 ግዙፍ ኮንትራቶች ከዚህ በፊት ያከናወነ መሆን አለበት |
| UNDP-SEEDS-03-2020 | የሚድያ አየር ሰዓት ምደባ አገልግሎቶች | የመራጮች ትምህርት የቲቪና ራዲዮ ማስታወቂያዎችን በመጠቀም ሃገር አቀፍ ቅስቀሳዎች ማድረግን ይጠይቃል። ለዚህ ደግሞ በራዲዮና ቲቪ ላይ የአየር ሰዓት መግዛት ያስፈልጋል። | • ቢያንስ የ3 ዓመት ልምድ ያለው<br>• በሁሉም ዋና ዋና የቲቪና ራዲዮ ጣቢያዎች (የማህበረሰብ ራዲዮ ጣቢያዎችን ላይ የአየር ሰዓት የማግኘት ቴክኒካዊ አቅም ሊኖረው ይገባል<br>• ከ $ 50,000 (ሃምሳ ሺህ ዶላር) በላይ ዋጋ ያላቸውን 3 ግዙፍ ኮንትራቶች ከዚህ በፊት ያከናወነ መሆን አለበት |
| UNDP-SEEDS-04-2020 | በመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ ቅስቀሳዎችን መከታተል | በቲቪ፣ ራዲዮና የሕትመት ሚድያዎች ላይ የሚተላለፉ ሃገር አቀፍ የመራጮች ማስተማሪያ ቅስቀሳዎች ትክክለኛነታቸውንና ጥራታቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል ክትትል ሊደረግባቸው ይገባል። | • ቢያንስ የ3 ዓመት ልምድ ያለው<br>• የተገዙ የማስታወቂያ ቦታዎች ላይ ክትትል የማድረግ የቴክኒክ ብቃት ሊኖረው ይገባል።<br>• ከዚህ በፊት የተከናወኑ ሐገር አቀፍ ቅስቀሳዎች ናሙና ጥራት<br>• ከ $20,000 (ሃያ ሺህ ዶላር) በላይ ዋጋ ያላቸውን 3 ግዙፍ ኮንትራቶች ከዚህ በፊት ያከናወነ መሆን አለበት |
| UNDP-SEEDS-05-2020 | የጥሪ ማዕከልና የአጭር የጽሑፍ መልዕክት አገልግሎቶች | የጥሪ ማዕከላትና የአጭር የጽሑፍ መልዕክት አገልግሎቶች በሐገር አቀፍ ደረጃ መረጃን ለማጋራትና ለማሰራጨት ወሳኝ መንገዶች በመሆናቸው የመራጮች ትምህርት አካል ሆነው ያገለግላሉ። | • ቢያንስ የ3 ዓመት ልምድ ያለው<br>• የጥሪ ማዕከላትን ለማቋቋም የሚያስችል የቴክኒክ ብቃት ያለው<br>• 3 ሐገር አቀፍ የጥሪ ማዕከላትን ያስተዳደረ መሆን አለበት |
| UNDP-SEEDS-06-2020 | የማሕበራዊ ሚድያ አገልግሎቶች | ማሕበራዊ ሚድያ በፍጥነት በሚዘዋወር የመረጃ ፍሰት ውስጥ ለመራጮች መረጃ በመስጠት ረገድ ወሳኝ ሚና ይጫወታል። Twitter, Facebook, WhatsApp, ኦንላይን ማስታወቂያዎችና ሌሎች መድረኮች መረጃን ለማሰራጨት ጥቅም ላይ የሚውሉበት መጠን እየጨመረ መጥቷል። | • ቢያንስ የ2 ዓመት ልምድ ያለው<br>• የማሕበራዊ ሚድያ ቅስቀሳዎችን ለማካሄድ ቴክኒካዊ ብቃት ያለው<br>• ማሕበራዊ ሚድያን ለመከታተልና ለመተንተን የሚያስችል ቴክኒካዊ ብቃት ያለው<br>• ከዚህ በፊት ሐገር አቀፍ የማሕበራዊ ሚድያ ቅስቀሳዎችን ያስተዳደረ መሆን አለበት |
| UNDP-SEEDS-07-2020 | የመዝናኛ አገልግሎቶች | መራጮችን ማስተማር የፊት ለፊት ቅስቀሳዎችን የሚፈልግ ሲሆን እነዚህ ቅስቀሳዎችም ቴአትሮችን፣ ዘፋኞችን፣ አርቲስቶችንና ድራማን በመጠቀም መራጮችን ለምርጫ ለመቀስቀስ ያስችላሉ። ይህ ደግሞ ቲቪ፣ ራዲዮ እና ማሕበራዊ ሚድያን የመጠቀም ዕድል የሌላቸውን የገጠር ነዋሪዎች ለመድረስ ውጤታማ መሳሪያ ነው። | • ቢያንስ የ3 ዓመት ልምድ ያለው<br>• ድራማና ቴአትርን በክልላዊ ቋንቋዎች ለማዘጋጀት የሚያስችል አቅም ያለው<br>• የሃገር ውስጥ አርቲስቶችንና ዘፋኞችን ለመቅጠር የሚያስችል የማኔጅመንት አቅም ያለው<br>• ከዚህ በፊት ዋጋቸው USD 20,000 (ሃያ ሺህ ዩኤስ ዶላር) የሆኑ ቢያንስ 3 ኮንትራቶችን የፈጸመ መሆን አለበት |
| UNDP-SEEDS-08-2020 | የሕዝብ አስተያየት መሰብሰቢያ የዳሰሳ ጥናቶች | የሕዝብ አስተያየት መሰብሰቢያ የዳሰሳ ጥናቶች የመራጮችን ጉዳዮችንና የሕዝባዊ መረጃ መጠንን በተመለከተ ግንዛቤን የሚያስጨብጡ ሲሆን የመራጮች ትምህርት ዘመቻዎች በተሻለ ዒላማቸውን እንዲያገኙ ለማድረግ ያስችላል። | • ቢያንስ የ2 ዓመት ልምድ ያለው<br>• ሐገር አቀፍ የዳሰሳ ጥናቶችን ለማካሄደ የሚያስችል ቴክኒካዊ አቅም ያለው<br>• ከዚህ በፊት ቢያንስ 3 ሐገር አቀፍ የዳሰሳ ጥናቶችን ያስተዳደረ መሆን አለበት |
| UNDP-SEEDS-09-2020 | የኤቨንት ማኔጅመንትና ትግበራ | የፕሮግራም ማኔጅመነት፣ ዲዛይንና የሕትመት አገልግሎቶችን (ለምሳሌ፡ ባነሮች)፣ የመስተንግዶ አገልግሎት፣ ለአንድ አገልግሎት የተመደቡ ፋሲሊቲዎችን | • ቢያንስ የ3 ዓመት ልምድ ያለው<br>• መጠነ ሰፊ የሆኑ ዝግጅቶችን (ኤቨንቶችን) ለማካሄድና ለመቆጣጠር ቴክኒካዊ ብቃት ያለው |

| | | | |
|---|---|---|---|
| | | ማስተዳደር፣ ፋሲሊቲዎችን ለፕሬስ ዝግጅቶች ማመቻቸትና ኦዲዮ ቪዥዋል ዝግጅትን ጨምሮ ግዙፍ የሆኑ ኤቨንቶችን ማስተዳደር። | • ቢያንስ የአንድ ሳምንት ቆይታ ያላቸውንና ሐገር አቀፍ ፕሬስን ያሳተፉ ቢያንስ 3 ግዙፍ ኤቨንቶችን (ከ1000 በላይ ተሳታፊ ያላቸው) የመራ መሆን አለበት<br>• ታዳሚውን ለመሳብና ለማሳተፍ የሚያስችሉ ፈጠራዊ ሃሳቦችን የመጠቀም ልምድ።<br>• ኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙትን ሁሉንም ክልሎች የመድረስ አቅም ያለው መሆን አለበት። |
| UNDP-SEEDS-10-2020 | የሰው ሐይል አስተዳደር | ምርጫዎች በሚካሄዱበት ወቅት መጠነ ሰፊ የሆነ ሰራተኞችን የመቅጠር ስራ መስራት ያስፈልጋል፤ ይህ ደግሞ በስራው ስፔሻላይዝ ያደረጉ ድርጅቶች በሒደቱ ላይ ግልጽነትን፣ የተቀመጡ መስፈርቶችን የሚያሟሉ ሰራተኞች መቀጠራቸውን እንዲያረጋግጡ፣ የጥራት መስፈርቶችን እንዲያከብሩና የሰው ሐይል አስተዳደር እንዲያከናውኑ ይጠይቃል | • ቢያንስ የ2 ዓመት ልምድ ያለው<br>• መጠነ ሰፊ የሆነና ክልላዊ ሽፋን ያለው የሰው ሐይል አስተዳደር የማከናወን ቴክኒካዊ ብቃት ያለው<br>• ዋጋቸው USD 20,000 (ሃያ ሺህ ዶላር) የሆነ ቢያንስ 3 ታላላቅ ኮንትራቶችን የመራ መሆን አለበት |
| UNDP-SEEDS-11-2020 | አይሲቲ አገልግሎቶች | በምርጫዎች ወቅት፣ በሐገር አቀፍ፣ ክልል አቀፍና በዞን ደረጃ የአይሲቲ አገልግሎቶችን ለማቅረብ አስፈላጊ ይሆናል፤ በዚህም ውስጥ የኮኔክቲቪቲ፣ የድጋፍና የአመራር አገልግሎቶች፣ ስልጠና፣ ወዘተ… ይገኙበታል። | • ቢያንስ የ5 ዓመት ልምድ ያለው<br>• በሐገር አቀፍ፣ ክልል አቀፍና በዞን ደረጃ የአይሲቲ አገልግሎቶችን ለማቅረብ የሚያስችል ቴክኒካዊ ብቃት ያለው<br>• ዋጋቸው USD 50,000 (ሃምሳ ሺህ ዶላር) የሆነ ቢያንስ 3 ሐገር አቀፍ ታላላቅ ኮንትራቶችን የመራ መሆን አለበት |
| UNDP-SEEDS-12-2020 | የሎጂስትቲክ አገልግሎቶች | ምርጫ መጠነ ሰፊ የሆነ የሎጂስቲክ ስራዎችና አገልግሎቶችን ይጠይቃል። በመጋዘን እና ሎጂስቲክ አስተዳደር ላይ ልምድ ካላቸው ድርጅቶች አገልግሎት ማግኘት የሚያስፈልግ ሲሆን፣ በዚህም ውስጥ በሐገር አቀፍና ክልል አቀፍ ደረጃ የመጋዘን ፋሲሊቲዎችን ማቅረብ ይገኝበታል። | • ቢያንስ የ5 ዓመት ልምድ ያለው<br>• ግዙፍና ውስብስብ የሎጂስቲክ ኦፕሬሽኖችን ለማከናወን የሚያስችል የቴክኒክ አቅም ያለው<br>• ዋጋቸው USD 50,000 (ሃምሳ ሺህ ዶላር) የሆነ ቢያንስ 3 ሐገር አቀፍ ታላላቅ ኮንትራቶችን የመራ መሆን አለበት |

***<u>መቅረብ ያለባቸው ደጋፊ ሰነዶች</u>***

ፍላጎቱ ያላቸው አመልካቾች የፍላጎት መግለጫውን ለመመዘን ቢያንስ የሚከተሉትን አስገዳጅ መስፈርቶች ማሟላት አለባቸው፡-

- ***ድርጅቱ በሃገር ውስጥ ለመስራትና ግብር ለመክፈል በሕጋዊነት የተመዘገበ ስለመሆኑ ማስረጃ (የተ.እ.ታ ምዝገባ፣ የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር)***
- ***የድርጅቱን የስራ ልምድና የማኔጅመንት መዋቅር የሚያሳይ ፕሮፋይል***
- ***ያለፉት 2 ዓመታት ኦዲት የተደረጉ የፋይናንስ ሰነዶች (የሒሳብ መግለጫዎች)***
- ***የማቴሪያሎች፣ ዲዛይኖችና ፕሮዳክሽን ናሙናዎች***
- ***ድርጅቱ የተጠየቁትን አገልግሎቶች ከማቅረብ አንጻር ያለው አቅም በሰራተኞች ብዛትና በፕሮዳክሽን የተረጋገጠ አጠቃላይና ተዛማጅ የስራ ልምድ፡- የፕሮጀክቶች ማጣቀሻ ዝርዝር።***
- ***ሌሎች አግባብነት ያላቸው ደጋፊ ሰነዶች***

***<u>የቅድመ ማጣሪያ መስፈርቶች</u>***

**ከዩኤንዲፒ ጋር ለመስራት ብቁ ስለመሆን**

አቅራቢው ድርጅት የተቀመጡለትን የብቁነት መስፈርቶች ማሟላት ያለበት ሲሆን፣ ከአልቃኢዳ ጋር ግንኙነት አላቸው ተብለው በ UN SC 1267/1989 የተዘረዘሩ ድርጅቶች ውስጥ ወይም ሌላ የተመድ ብቁ የማያደርግ ዝርዝር ውስጥ መስፈር የለባቸውም። የተመድ የአቅራቢዎችን የስነ-ምግባር ደንብ ማክበርና የዩኤንዲፒ የፀረ ማጭበርበር ፖሊሲን መቀበል ያስፈልጋል።

**ተዛማጅ ፕሮፋይል፣ ግብዓቶችና የስራ ልምድ**

አቅራቢው ድርጅት ለፍላጎት መግለጫውና ለጨረታ ግብዣው ሙሉ በሙሉ ተዛማጅነት ያላቸውን በቂ አቅሞች (አደረጃጀት፣ ሐብቶች፣ የሰው ሐይል፣ ግንዛቤ፣ መሳሪያዎችና ሲስተሞች፣ ወዘተ…) እንደዚሁም በቂ የስራ ልምድ ያለው መሆኑን በተግባር ማሳየት አለበት። ፍላጎቱ ያላቸው አቅራቢዎችና ተዛማጅ የስራ አጋሮች አቅማቸውንና ልዩ ችሎታቸውን/የበፊት የስራ አፈጻጸማቸውን በተግባር ማሳየት አለባቸው።

**የብቃት ማረጋገጫ**
አቅራቢውና የትኛውም የስራ አጋር (እና/ወይም ዋነኛ ንኡስ ኮንትራክተር) በዚህ ጨረታ መሰረት ለሚቀርበው ዕቃ ወይም አገልግሎት ንቁ የሆነ የጥራት ማረጋገጫና የጥራት ቁጥጥር ስርዓት ሊኖረው ይገባል።

**የፋይናንስ ጥንካሬ**
አቅራቢው ድርጅት ከላይ ከተጠቀሰው ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውን ፕሮጀክቶች ለማከናወን የሚያስችል ጤናማ የፋይናንስ አቋምና የዕዳ አከፋፈል ሁኔታ ሊኖረው ይገባል።

**የፍ/ቤት ክርክር**
አቅራቢው ድርጅት ከላይ የተጠቀሰውን ዓይነት ፕሮጀክት በአግባቡ እንዳይፈጽም ሊያግደው በሚችል የትኛውም ዓይነት በሒደት ላይ የፍ/ቤት ክርክር (ግልግል፣ የካሳ ጥያቄ፣ ኪሳራ) ውስጥ ያለ መሆን የለበትም። ዩኤንዲፒ ማንኛውንም በተከታታይ የፍ/ቤት ክርክር ጉዳዮች ውስጥ የሚሳተፍ አቅራቢ ድርጅትን ያለመምረጥ መብቱ የተጠበቀ ነው።

**የኩባንያው አጋሮች (ወይም ማናቸውም ዋና ዋና ንኡስ ኮንትራክተሮች) በተመለከተ የሚከተሉት መረጃዎችና ማስረጃዎች መቅረብ አለባቸው፡-**

- *አጋሮችን የሚመለከቱ ዝርዝር መረጃዎች። አጋሮችን የሚመለከት መረጃን በሰነድ ማቅረብ፤ ለምሳሌ የድርጅቱን አቅም፣ የብቃት ማረጋገጫዎችና ሌሎች ማስረጃዎችን ጨምሮ የኩባንያው ፕሮፋይል።*
- *አቅራቢው ድርጅት ዕቃዎች/ማቴሪያሎችን በጥራትና በወቅቱ ለማስረከብ ከአጋሮች ጋር ለመሳተፍና ግንኙነቶችን ለማስተዳደር ያስቀመጣቸው መስፈርቶችና ግብዓቶች።*
- *ከሁሉም የተዘረዘሩ አጋሮች ጋር ያለን ግንኙነት የሚያሳዩ ሰነዶች፤ ለምሳሌ የአጋርነት ስምምነቶች፣ ውክልና፣ የፈቃድ ደብዳቤዎች፣ ወዘተ…*

ፍላጎቱ ያላቸው ድርጅቶች አገልግሎቶቹን ለመስጠት ብቃት ያላቸው መሆናቸውን የሚጠቁም መረጃ ማቅረብ አለባቸው። ድርጅቶቹ የሚመረጡት በዩኤንዲፒ የግዥ መመሪያዎችና በዩኤንዲፒ የፋይናንስ ደንቦችና መመሪያዎች ውስጥ በተቀመጡት አሰራሮች መሰረት ነው።

የፍላጎት መግለጫውና አብረውት የሚቀርቡ ሰነዶች **እስከ ጃንዋሪ 20/2020 (ጥር 11 ቀን 2012 ዓ.ም.) ድረስ** “SEEDS Project EOI number” የሚል ጽሑፍ በተጻፈበት የታሸገ ኤንቨሎፕ ውስጥ ተደርገው መቅረብ አለባቸው። በኢሜይል ወይም በፋክስ የሚላኩ ሰነዶች ተቀባይነት የላቸውም። ከላይ ከተጠቀሰው ቀን በኋላ የሚቀርብ የፍላጎት መግለጫ ተቀባይነት አይኖረውም።

የተጠየቁትን መረጃዎች ያልያዘ የአቅራቢዎች የፍላጎት መግለጫ ሰነድ ውድቅ ይደረጋል። ***ወደ ጨረታው ሒደት የሚገቡት ድርጅቶች የጨረታ ሰነድ እንዲያቀርቡ የተጋበዙት ብቻ ናቸው።*** የጨረታ ግብዣ እና የትኛውም ተከታይ የግዥ ማዘዣ ወጪ የሚደረገው በዩኤንዲፒ ደንቦችና አሰራሮች መሰረት ነው።

ይህ የፍላጎት መግለጫ በዩኤንዲፒ ላይ የፋይናንስም ሆነ ሌላ ግዴታን አያስከትልም። ዩኤንዲፒ የትኛውንም የፍላጎት መግለጫ የመቀበል ወይም ያለመቀበል መብት ያለው ሲሆን ይህን ያደረገበትን ምክንያትም ለሚመለከተው አመልካች የማሳወቅ ግዴታ አይኖርበትም።

ከኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጋር እየሰሩ ያሉ እንደ IFES እና ECES ያሉ ሌሎች አጋር ድርጅቶች ከኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ጋር ለማከናወን ላቀዷቸው ስራዎች የቅድመ ማጣሪያውን ያለፉ ድርጅቶችን ለመምረጥ ተመሳሳይ ሒደትን ለመጠቀም ይችላሉ።

ፍላጎቱ ያላቸው ድርጅቶች ከታች በተገለጸው አድራሻ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይችላሉ፡-

**ለጥያቄ/ማብራሪያ**
info.procurementet@undp.org
የኢሜይሉ ርዕስ፡ SEEDS EOI- request for clarification

**የሰነዶች አቀራረብ**
ሁሉም ሰነዶች በሕትመት መልክ መቅረብ ያለባቸው ሲሆን፣ የናሙና ስራዎች ደግሞ በአካል እና/ወይም በፍላሽ ዲስክ መቅረብ አለባቸው
ሰነድ የማስገቢያ አድራሻ፡-
Supporting Elections for Ethiopia’s Democratic Strengthening (SEEDS)
የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የልማት ፕሮግራም
ቂርቆስ ክ/ከተማ፣ ቀበሌ 17/18፣ የቤት ቁ. 242፣ መ.ሳ.ቁ 406
የቀድሞው ኤሪክሰን ሕንጻ፣ 1ኛ ፎቅ፣ ከሳሊኒ ኮንስትራክሽን ፊት ለፊት/የኢሲኤ 3ኛ በር